# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 18 መስከረም 8 2001 ዓ.ም

## በታጠቁ ሀይላት የሚፈፀመው የደፈጣ ጥቃት ቀጥሏል

ነሐሴ 21 ቀን 2000ዓ.ም ከምሽቱ በሶስት ሰዐት ከዝዋይ ወደ አዲስ አበባ ሲሄድ የነበረ የፖሊስ ፓትሮል ቡድን ላይ የደፈጣ ጥቃት ደረሰ፡፡ ለዝግጅት ክፍላችን በቅርቡ የደረሰን ዜና እንደሚያመለክተው በዚህ ጥቃት መኪናዋ ከጥቅም ውጭ ስትሆን በውስጡ የነበሩ 2 ወታደሮች ላይ ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ ደርሶአል፡፡ በማግስቱም ነሐሴ 22 ቀን በአንድ ላንድ ክሩዘር ተጭነው ሲጉዋዙ የነበሩ የወያኔ/ኢሕአዴግ ታጣቂ አባላት ላይ መቂ በተባለ ስፍራ ተመሳሳይ የደፈጣ ጥቃት ተሰንዝሮአል፡፡ በጥቃቱ መኪናዋ ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ስትሆን ፤በውስጡዋ ከነበሩ ሓላፊዎች መሀከል ሶስቱ ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡ ጥቃቱን ያደረሱት ታጣቂዎች ማንነታቸው ያልታወቀ ሲሆን ፤ በብዙዎች ዘንድ ከወራት በፊት በሰሜን ሸዋ የተደረገውን ጥቃት ያደረሱት ሀይሎች ሳይሆኑ አይቀሩም የሚል ግምት አሳድሮአል፡፡

የመለስ አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጉልበት ለብዙ አስርት ዐመታት እገዛለሁ ብሎየሚያደርገው ከንቱ ሙከራ በሁሉም አቅጣጫ ፈተና እየገጠመው ነው፡፡በሶማልያ ያለውአለመረጋጋት እየፈጠረ ካለው ውጥረትና የወታደሩ ከፍተኛ ሀይል በኦጋዴን፤በሶማልያና፤በኤርትራ ድንበር እንደ ዘር ተበትኖ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት፤ በወትሮው ከሚታወቁት ታጋይድርጅቶች በተጨማሪ በትናንሽ ቡድኖች ተደራጅተው ፈጣንና በመሀል አገር የሚደረጉእንቅስቃሴዎች እየተጠናከሩ መምጣታቸው ታውቋል፡፡ ባለፉት ሁለት ወራት በሰሜን ሸዋ ውስጥበተለያዩ ከተሞች (መራኛ፤ ዐለም ከተማ፤ ሸዋ ሮቢት… ወዘተ) ለጊዜው ማንነታቸው ባልታወቀ ሀይላት የታጠቀ እንቅስቃሴ መደረጉን፣ እነኝህም ራሳቸውን" የ አንድነት ሀይሎች" ብለው የሚጠሩት የታጠቁ ሀይሎች ለሰዐታት ከተሞቹን ተቆጣጥረውሕዝቡን ስለትግላቸው አስተምረው በሲቪሉ ሕብረተሰብ ሕይወትም ሆነ ንብረት ላይ ምንም አደጋ ሳያደርሱ ከተሞቹን ለቅቀው መውጣታቸውን የተለያዩ የዜና አውታሮች መዘገባቸው ይታወሳል፡፤

## መለስ፤ የፖሊሲያቸውን ውድቀት በደሀ ሰራተኞች ላይ ለማላከክ ሞከሩ

### የብአዴኑ ተፈራ ዋልዋና የህወሀቷ ነፃነት አስፋው ከቦታቸው ተነሱ

በአዋሳ ከተማ እየተካሔደ ባለው የኢህአዴግ 7ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ፤ መለስ ዜናዊ በጠቅላላ አገሪቱ የሚገኙትንና ወደ 16 ሽህ እንደሚቆጠሩ የሚገመቱትን የግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች" ለሥራቸው ታማኝ ያልሆኑ" እና " ለአርሶ አደሩ ፍቅር የሌላቸው" በማለት በጅምላ ዘለፉ።በግብርና ምርት ፈጣን ዕድገት አስመዘገብን ሲሉ እና በባዶ ሜዳ ሲመፃደቁ የነበሩት መለስ፤ እውነታው እየፈጠጠ ገበሬው በገፍ በረሀብ ማለቅ ሲጀምር፤ በድሆቹ የግብርና ሠራተኞች ላይ የስድብ አፋቸውን ቢያላቅቁም ከተጠያቂነት የሚያስመልጣቸው እንዳልሆነ ጉባዔውን በቅርበት እየተከታተሉ ያሉ ታዛቢዎች ያደረሱን መረጃ ያመለክታል።ታዛቢዎቹን እጅግ ያስገረመው፤መለስ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎቹን በጅምላ የሰደቡዋቸው፤በተለያዩ መስኮች እየተማሩ ዲፕሎማ ለማግኘት ነው ትኩረት የሚያደርጉት በሚል ምክንያት መሆኑ ነው።፣ወደገጽ 4 ዞሯል.፣

## አቶ አማረ አረጋዊ ገና ፍርድ ቤት ይቀርባሉ

### ከዳሽን ጋር ያለው ሽኩቻ ከማስታወቂያ ጋር የተያያዘ መሆኑ ተጋለጠ

ሪፖርተር ጋዜጣ ከዳሽን ቢራ ፋብሪካ ጋር ከፍ ያለ መካረር ደረጃ የደረሰበት አለመግባባት መንስዔው ፤ ማስታወቂያ በመከልከሉ መሆኑን የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ስራ አስኪያጅ አጋለጡ።ስራ አስኪያጁ አቶ ብርሀኑ አድማሱ የሪፖርተር እህት ሚዲያ ለሆኑት የኢህአዴግ ልሳናት በሰጡት ቃለ ምልልስ እንደገለፁት፤ አቶ አማረ በተከሰሱበት ጉዳይ በፖሊስ ተይዘው ቃላቸውን ከሰጡ በሁዋላ በዋስ ተለቀቁ እንጂ፤እርሳቸው በጋዜጣቸው እያጮበረበሩ እንደሚፅፉት ከክሱ ነፃ ሆነው አልተሰናበቱም። ፖሊስ ቃላቸውን ከተቀበለ በሁዋላ ጉዳዩን ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ ለዐቃቤ ህግ እንደመራው የተናገሩት የፋብሪካው ወኪል ከሳሽ፤ ዐቃቤ ህግ ፋይሉን ወደ ፍርድ ቤት ልኮ ገና በፍርድ ቤት ውሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ነፃ እንደሆኑ አድርገው መፃፋቸው ስህተት ነው ብለዋል።

ስራ አስኪያጁ አያይዘውም የፋብሪካውና የሪፖርተር ጋዜጣ አለመግባባት አዲስ የተከሰተ ክስተት ሳይሆን ከስድስት ዓመት በፊት የተፈጠረ መሆኑን አመልክተዋል።"ሪፖርተሮች የዛሬ ስድስት አመት አካባቢ ያለ ፋብሪካው ፈቃድ አንድ የሽያጭና የማስታወቂያ ሠራተኞችንን በማጭበርበር ማስታወቂያ አውጥተው የክፍያ ገንዘብ ጠየቁን" ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ እኛም ያለፈቃዳችን ለወጣው ማስታወቂያ ክፍያ ከፈፀምን በሁዋላ፤ ዳግመኛ በሪፖርተር ጋዜጣ ማስታወቂያ ላለማውጣት ወሰንን" ብለዋል። እንደ ስራ አስኪያጁ ገለፃ፤ ሪፖርተር የጋዜጠኝነትን ስነ ምግባር በሚፃረር መልኩ በፋብሪካው ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ የከፈተው ከመሬት ተነስቶ በድንገት ሳይሆን፤የቆየው ቂም አዘል ቁስሉ አገርሽቶበት ነው።፣ወደገጽ2 ዞሯል፣

### የግንቦት 7 ንቅናቄ አጭር ሞገድ ሬድዮ ስርጭት

### መስከረም 1፣ 2001 ዓም ጀምሯል

**ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ።**

የህዝብ ግንኙነት ክፍል

# ርእሰ አንቀጽ

## በ ቢ . ፒ. አር. ስም በመንግስት ሠራተኞች ላይ የሚደረገው ዕመቃ ይቁም

ቢ . ፒ. አር. ይባላል አዲሱ ዘመናዊ የሥራ አደረጃጀት መንገድ :: ቢዝነስ ፕሮሰሰስ ሪኢንጂነሪንግ ማለት ነው:: የሠለጠነው አለም ድርጅቶች ግብአቶችን ከሰው ሃይል ጋር አቀናጅተው ለበለጠ ምርታማነት የሚንደረደሩበት የአሠራር ዘይቤ ነው :: ቢ . ፒ. አር. በበለፀገው አለም ድርጅቶች ፤ወጪን ቀንሰው፤ ጥራትን አሻሽለው፤ ምርታማነትን ጨምረው፤ ፈጣን አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚጠቀሙበት የአደረጃጀት መርህ ነው :: የአቶ መለስ አእምሮ ሲነከው ግን ፤ ከነዚህ አንዱንም ለመሆን አልቻለም :: ከፈረንጆቹ የተቀዳ ፤ ወይም ፈረንጆቹን ለመሸወድ ያለመ ሆኖ ግን ድብቅ አጀንዳ አለው :: የማፅዳት :: ቢ . ፒ. አር. ለግንቦት 97 ውርደቱ መልስና እብሪት ሽፋን ሆኖ ነው የቀረበው :: በ ቢ . ፒ. አር. ስም ሠራተኞች ለአመታት ካገለገሉበት ሥራቸው ይባረራሉ ፤ የወያኔን ፓርቲ አባልነት አልቀበል ያሉ ምሁራን ይፈናቀላሉ ፤ በአንፃሩ በሥነ ምግባርም በዕውቀትም ድሀ የሆኑ በሥልጣን ላይ ይቀመጣሉ :: ጥያቄው ይህን ማድረግ ለምን አስፈለገ ነው?

በመጀመሪያ ያው ለጋሽ ከሚባሉት ምዕራባውያን የሚላስ የሚቀመስ ፍርፋሪ ስለሚገኝበት «መንግስተዊ ሥርአታችንን ከሠለጠነው አለም ጋር ለማቀራረብ» ተብሎ የፕሮጅክት ገንዘብ ይገኝበታል :: « ቢሮክራሲው 65 በመቶ አማራ ነው እንመነጥረዋለን» ሲሉ ለከረሙት ዘመቻቸው ጠቃሚ ሆኖ መገኘቱ ግን የበለጠው ምክንያት ነው :: አዲስም አይደለም :: ሠልጥነውበታል :: ገና ከጫካ እንደመጡም የአለም ባንክን «ሪ ስትራክቸሪንግ» ለዚሁ ዘረኛ አላማ ተጠቅመውበት እንደነበር ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው :: ግር የሚለው ግን ፤ እሺ ያኔስ ለታጋዮቻቸው የሥራ እድል መክፈት ስለነበረባቸው ፤ የደርግ አፋሽ አጎንባሽ የነበሩትንም ከመንግስት ሃላፊነት ቦታ ለማንሳት ያስፈልጋቸው ይሆን ነበር ብለን የመጠራጠር ዕድል ብንሰጣቸው እንኳዋን ፤ የዛሬውን እንዴት እንረዳው? በብዙ መሥሪያ ቤቶች በ ቢ . ፒ. አር. ስም መለስ ወንጀል እየፈፀመ ነው :: «ለኔ ፓርቲ መስመር ያልንተበረከከ ሁሉ ይራባል» ብሎ እየፈከረ ነው ::

በየትም ሃገር የፖለቲካ መስፈርት የሚደረግባቸው የሥልጣን እርከኖች አሉ :: ባብዛኛው ከዲሬክተር ሥልጣን በላይ ያሉ ቢሮዎች በሥልጣን ላይ ባለው ፓርቲ ሊወከሉ ይችላሉ :: ሙሉውን የመንግስት ቢሮክራሲ በፓርቲ አባላቶቼ አስይዛለሁ የሚለው ሙከራ ግን ፤ ከሂትለር ወዲህ የመለስ እብደት የመጀመሪያው መሆኑ ነው :: ከሂትለርም ሙከራ ግን የመለስን ይበልጥ አስቀያሚ የሚያደርገው ፤ ከፍተኛው የሥልጣን እርከን የሚታደላቸው ሰዎች የአንድ ፓርቲ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ከተወሰነ ጠባብ መንደር የመጡ መሆናቸውም ጭምር ነው ::

መለስ ይህን ሁሉ ክፋትና ጭከኔ ለማድረግ የተገደደውም ፤ በግንቦት 97 ከህዝብ የነጠቀውን ሥልጣን ለመከላከል ብሎ ነው :: የመረጠው መስመር ራሱንና ቡችሎቹን ይበልጥ ወደገደል ፤ ይበልጥም ወደወንጀል የሚከተቸው ነው :: ኢትዮጵያውያን የመንግስት ሠራተኞች በሃገራቸው ላይ የትኛውንም ፓርቲ ለመወገን ሳይገደዱ፤ በዕውቀታቸውና በጉልበቸው አገልግለው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የመጥቀም መብት አላቸው :: የመንግስት ሠራተኞች ቁጥጥር በሌላቸው ብሄረሰባዊ ማንነተቸው የተነሳ፤ ማንም ጊዜ ያነሳው ቅል የሚሰብራቸው ድንጋዮች አይደሉም :: እምቢ ለማንነተችን ፤ እምቢ ለልጆቻችን፤ እምቢ ለመብታችን ብለውም ከሥርአቱ ጋር ተናንቀው ቢሞቱ የሚጠብቃቸው የታሪክ ባለቤትነትና ትልቅነት እንጂ ነው ::

## አቶ አማረ አረጋዊ ገና ፍርድ ቤት ይቀርባሉ

ከገጽ 1 የዞረ

እየሰሩት ያለው ስራ፤ ስነ ምግባርንም ሆነ ህግን የጣሰ ስለሆነ እንዲታቀቡ በግለሰብ ደረጃ ሳይቀር ለአቶ አማረ ነግረዋቸው እንደነበር የገለፁት ስራ አስኪያጁ፤ ሊታረሙ ባለመቻላቸው ወደ ህግ ለመሄድ መገደዳቸውን አስረድተዋል።የመንግስት ድርጅት የስራ ሀላፊዎችን ሳይቀር በማስፈራራት ከመንግስት ተቋማት የማስታወቂያ ገንዘብ በማጋበስ የሚታወቁት አማረ፤ከዳሽን ቢራ ጋር ስለገቡበት ውዝግብ ቃለ ምልልስ ሲሰጡም ሆነ በጋዜጣቸው ላይ ሲፅፉ፤ ለፋብሪካው ሰራተኞች የተቆረቆሩ ለመምሰል ያደረጉት ጥረት በሚያውቋቸው ዘንድ ፈፅሞ የማይዋጥ እንደነበረ ሁሉ፤ ዛሬም የፋብሪካው ስራ አስኪያጅ እውነታውን ሲያወጡት የተገረመ የለም።ቀደም ሲል ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሪፖርተር ጋዜጣ ጋዜጠኛ የሆነውና ይህን ጉዳይ የዘገበው ተሾመ ንቁ ፤ በተመሳሳይ ጎንደር ድረስ ተወስዶ ሲታሰር ፤ ሪፖርተር ጋዜጣም ሆነ ሌሎችም ደጋፊዎቹ ምንም አለማለታቸውንና ጋዜጠኛው ስለመታሰሩም የተሰማ ድምፅ እንዳልነበረ ያስታወሱት ስራ አስኪያጁ ፤ ዛሬ አማረ ሲታሰር ከራሱ ከሪፖርተርም ሆነ ከጥቂት ደጋፊዎቹ ጩኸት መሰማቱ እንደገረማቸው በመግለፅ ፤ ሰብዐዊነትን እና ህግን ተንተርሰው ሳይሆን፤ዝምድናቸው ከንክኗቸው ሲንጫጩ ለሰነበቱት ጠባቦችና ጋዜጠኛ ተብየዎች በተዘዋዋሪ መንገድ መልዕክት አስተላልፈውላቸዋል።

በእርግጥም እነዚህ ወገኖች፤ ጋዜጠኞችን ጨምሮ ስንት ዜጎች በፍትህ እጦት ለዐመታት በሚንገላቱባትና በፖሊሶች ያለጥፋታቸው በሚጠፈጠፉባት አገር ፤ እንደሽርሽር ለሶስት ቀናት ጎንደር ደርሶ የተመለሰው አማረ፤ እንዴት በከሳሽ መኪና ይወሰዳል ? እንዴት ያለ መጥሪያ ፖሊስ እጁን ይነካዋል? ብለው ይህን ያህል ሰማይ የተከነበለ ያህል እግዚኦ ማለታቸው ለብዙዎቻችን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው ይላሉ ታዛቢዎች።አማረ ከህግ በላይ እንደሆነ ወይም ህግ ለነአማረ ብቻ ጥብቅና እንዲቆም ተፈልጎ "ከነኩት አትበሉን የሹም ዶሮዎች" ይህን ያህል እሪታ መሰማቱ ፤ አንደኛው የአገሪቱ የፍትህ ህመም ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል መሆኑንም አስረድተዋል።ሆኖም አቶ አማረ በዚህ ጉዳይ በመጠኑም ቢሆን የቀመሱት፤ ከፋብሪካው ጀርባ አለቃቸው በረከት መኖራቸውን እያወቁ፤ በሌሎች እንደለመዱት ከአቅም በላይ በመንጠራራታቸው ነው የሚሉት አስተያየት ሰጭዎች፤የፋብሪካው ቦርድ ሰብሳቢ እንደ አቶ በረከት የማዘዝ ጉልበት የሌለው የስም ባለስልጣን ቢሆን ኖሮ፤ባለፉት ስድስት ዐመታት ራስ አማረ በተካኑበት በፍርሀት የማሸማቀቅ ታክቲክ፤ በትንሹ በማስታወቂያ ስም መቶ ሽህ ብሮችን ያስገብሩ ነበር ሲሉ አስተያየታቸውን ደምድመዋል።



የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## ቆይታ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር (የመጀመሪያ ክፍል)

ይህ ቃለ ምልልስ ከግንቦት 7 ድምጽ የራድዮ ጣቢያ የተወሰደ ነው።የግንቦት ሰባት ድምጽ አንዱ የተመሰረተበት አላማ፣ ለህዝብ መረጃ ማቅረብና የህዝብ ነጻ አንደበት መሆን በተጨማሪም ፣ የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የፖለቲካ አላማ ምን እንደሆነ በሃገር ውስጥ ላለውና ከሀገረ ውጭ በአለም ዙሪያ ተበትኖ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ማስተዋወቅ ነው። የግንቦት ሰባት ድምጽ ሬድዮ ጣቢያ፣ የንቅናቄውን አላማ የኢትዮጵያውያን ሁሉ አላማ እንዲሆን ማድርግ፣ ኢትዮጵያውያን በያሉበት የንቅናቄውን አላማ ደግፈው ትግሉን እንዲቀላቀሉ፣ ሁላችንም መክፈል የሚገባንን መስዋእትነት በየፈርጁ ከፍለን፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ግፍን፣ በሃገራችን ላይ ውርደትን እያመረተ ያለውን የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ፣ እስካሁን ካደረሳቸው ክፍተኛ በደሎች በተጨማሪ ሌሎች በደሎች ሳይፍጽም በአስቸኳይ ለማስወገድ ንቅናቄው የጀመረውን ትግል ማገዝ ነው።

ይህንን ለማሳከት ግን፣ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ማንነቱን ለኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ ማስተዋወቅ አለበት። በንቅናቄው እይታ፣ "የግንቦት 97 ምርጫ ያረጋገጠው አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱን ህይወትና የሃገሩን ጉዳይ በሚመለከት የሚቀርብለትን አስተያየት ማዳመጥ መመርመር ይጠቅመኛል ብሎ የሚያስበውን ነገር መምረጥ እንደሚችል ነው" ብሎ ያምናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚገኝበት አሰቃቂ ድህነት፣ ከጉስቁልናው፣ ከመጨቅጨቂት ለባሽነቱ፣ ከኖረበት የዘመናዊ ትምህርት እድል አልባ ህይወቱ ጋር ሲነጻጸር፣ እጅግ የሚያስገርም የፖለቲካ ብስለት ያለው ህዝብ መሆኑን በግንቦት 97 ምርጫ አረጋግጧል ብሎ የግንቦት 7 ንቅናቄ ያምናል። "ከእዚህ ምርጫ በሁዋላ ማንም የፖለቲካ ድርጅት ይህንን ህዝብ እኔ አውቅልሃለሁ፣ ዝም ብለህ ተከተለኝ ሊለው አይችልም። ምንም አታውቅም እኔ ስለማውቅልህ ልግዛህ ሊለውም አይችልም፡፡ በግንቦት 7 1997 ምርጫ በተጨባጭ እንደታየው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን ሞግዚት የሚያስፈልገው የኢትዮጵያን ህዝብ እናውቀዋለን በማለት በስሙ የሚምሉ፣ ነገር ግን የኢትዮጵያን ህዝብ ብስለቱንና አዋቂነቱን ጨዋነቱንና ስልጡንነቱን ለመቀበል ወይም ለማየት በእብሪት የታወሩሩ በስልጣን ላይ ያሉ አማባገነኖችና አጫፋሪዎቻቸው ብቻ ናቸው ብሎ" የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በጥብቅ ያምናል። ከእዚህም እምነት በመነሳት ግንቦት ሰባት ንቅናቄ ደግፈኝ የሚል ጥሪ ለህዘብ ሲያቀርብ ለምን መደገፍ እንዳበት የህዝቡን ብስለትና አዋቂነት ግምት ውስጥ ያስገባ መግለጫ ማብራሪያ መስጠት አለብኝ ብሎ ያምናል። "የአለማ ግልጽነት አላማን ለማስፈጸም ለሚያስፈልገው የመንፈስ ጽናት መሰረት ነው" ከሚለው የንቅናቄው መርህ በመነሳት ህዝብ ለግንቦት 7 የሚሰጠው ድጋፍ፣ በግንቦት 7 ጥላ ስር ተሰባስነቦ የሚያደርገው ትግል በምክንያትና በእውቀት ላይ ተመስርቶ ሊደረግ ይገባዋል ብሎ ንቅናቄው ያምናል።

ይህንን ለማድረግ የግንቦት ሰባት ንቅናቄን ምንነት እንዴት እንደተመሰረተ ምን እያደረገ እንደሆነ፣ ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብና ቀስፎ የያዘውን ረሃብ በሽታ አፈናና ውርደት፣ እንዴት ማሰቆም ይቻላል ብሎ እንደሚያምን ንቅናቄው የመለስን ግፈኛ አገዛዝ የሚታገልባቸው ስልቶች ምን እንደሆኑ፣ለምን ንቅናቄው ብዙዎች ሞክረውት ውጤት ያላመጣን የፖለቲካ ትግል እኔ ውጤት አመጣለሁ ብሎ እንደሚያስብ ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሰለሚኖረው ግንኙነት ተባብሮ ሰለመታገል ያለውን አመለካከት ከአምባገናነዊ መንግሰት አፈቀላጤዎች ለሚወረወሩበት ክሶች ምን ምላሽ አለው።ከሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሚሰማቸውን ጭንቀትና የሚያስቧቸውን ጉዳዮች እንዴት ያያቸዋል፡፡ ለእነዚህስ ምን ምላሽ አለው፣ በሌሎቹም ጉዳዮች ላይ በየግዜው ከንቅናቄው አመራሮች ጋር ቃለ ምልልስ በማድረግ የእዚህን ንቅናቄ መሰረታዊ አላማዎችንና ራእዮች በሚገባ ህዝብ እንዲያውቃቸው እናደርጋለን፡፡ ቃል እንደገባነውም ከላይ ላነሳናቸውና ለሌችም ጥያቄዎች አስተያየቶት እንዲሰጡ የምንጠይቃቸውን የንቅናቄውን አመራሮች በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ እናንተን አደማጮቻችንን ሆነን አምረን እንጠይቃቸዋለን፡፡ እንግዲህ በእዚህ መንፍስ በተከታተይ የምናደርጋችውን ቃለ ምልሶች የምንጀምረው ከንቅናቄው አመራር ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር ይሆናል፡፡

ጥያቄ--ለምን ንቅናቄው ግንቦት ሰባት ተባለ፡፡ ለፖለቲካ ድርጅቶች እንዲህ አይነት የስም አሰጣጥ በሃገራችን ያልተለመደ ነው፡፡ በሃገራችን ታሪካዊና ፖለቲካዊ ትርጉም ያላቸው በርካታ ቀናቶች አሉ ከእነዚህ ሁሉ ለምን ግንቦት 7 ተመረጠ.፡፡

አቶ አንዳርጋቸው-አዎን እንዳልከው ያልተለመደ ስም አሰጣጥ ነው፡፡ ግንቦት ሰባትም እኮ በሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ያልተለመደ የፖለቲካ አላማ ይዞ የተነሳ ንቅናቄ ነው፡፡ልክ ነህ በሃገራችን በርካታ በጥሩም በመጥፎም በሃዘን በደስታ ወይም ሁለቱም በተቀላቀሉበት ሁኔታ የምናስታውሳቸው ቀናት አሉን፡፡ አብዘኛዎቹ ቀናት ግን የፖለተካ ንቅናቂያችን የቆመበትን መሰረታዊ አላማ የሚያንጸባርቁ አይደሉም፡፡ ንቅናቄያችን በእኛ እምነት ህዝብ በግንቦት 7 1997. ባሳየው፣ አውቀት ፣ብስለት ፣ ምኞት ፣ተስፋና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የቆመ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በእዛች እለት ከ26 ሚሊዮን በላይ ህዝብ፣ ቀደም ባሉት ወራት ባገኘው አጋጣሚ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ሲሰሩትና ሲናገሩት የነበረውን በአግባቡ አይቶና አዳምጦ፣ የተወሳሰበ የድምጽ አሰጣጥ ተስፋ ሳያስቆርጠው፣ ግራ ሳያጋባው በሚገባ አስቀድሞ አስቦና ተጠንቅቆ ለመጀመሪያ ግዜ በታሪኩ ያስተዳድሩኛል ብሎ ላመነባቸው ተመራጮች በድምጹ ውክልና የሰጠበት፣ መስጠት የሚችል መሆኑን ያረጋገጠበት፣ በረጅም ታሪኩ ለመጀመሪያ ግዜ ለይስሙላ ሳይሆን በተባጭ የህይወቱ የሃገሩ የወደፊት እጣው ጌታ ለመሆን እድል ተከፍቶ የነበረበትን፣ ይህንን እድልም በሚገባ መጠቀም የሚችል ህዝብ መሆኑን ያረጋገጠበት እለት ነው፡፡

ከምርጫው በኋላ የህዝብ ድምጽ ተሰርቆ፣ በህዝብ ላይ እልቂት ታውጆ ለግዜው ህዝብ የሃገሩና የገዛ ህይወቱ ባለቤት መሆን የሚቸልበት ዘመን የራቀ ቢመስልም፣ ግንቦት 7 የኢትዮጵያ ህዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ አላዋቂ ያልበሰለና ያልሰለጠነ አድረገው ሲቆጥሩት ለኖሩት ገዥዎቹ፣ ወይም ወደገዥነት ለማቆብቆብ ለሚመኙ የሃገሪቱ ልሂቃን ቁልጭ ያለ መልስ የሰጠበት እለት ነበር፡፡ የሚበጀኝን አውቃለሁ መወሰን መምረጥ እችላለሁ ከአሁን በኋላ እኔን ሳያሳትፍ የእኔ ፍላጎት ሳይጠየቅ እኔ ውክልና ሳልሰጠው ማንም አሰተዳድርሀለሁ፣ እገዛሃለሁ ማለት አይችልም የሚል ሃያል ድምጹን ሰላማዊና ሰልጡን በሆነ መንገድ የሰማበት ነው፡፡

ይህ መልእክት ሀገር በቀል ለሆኑ ሃይሎች ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ህዝብ ካለቸው ንቀት እየተነሱ በአፍሪካ ዴሞክራሲ አይሰራም፣ ህዝቡ የሚሻለው አንድ ጠንካራ አምባገን ቢመራው ነው፡፡ ዴሞክራሲ ቢባልም የእኛን የነጮቹን አይነት የተስተካከለ የተዋጣለት ነገር በሺህ አመትም ማየት ስለማይቻል፣ በምርጫ ወቅት ማጭበርበር ቢኖርም ትንሽ ግድያ እና እስራት ቢኖርም በአፍሪቃ ደረጃ የሚመጥን ዴሞክራሲ ስለሆነ የአፍሪካ ዴሞክራሲ ከእዚህ አያልፍም ብለን መቀበል ተገቢ ነው የሚል አመለካከት ለነበራቸው ነጮች መልሱን የሰጠበት ቀን ነበር፡፡ ግንቦት እንዲህ አይነት መሰረታዊ የሆነ ትርጉም ስላለው ነው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ይህንን ስም እኛ የመረጥነው፡፡

ይቀጥላል፣

# የፖለቲካ ትንትና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ጽናት እንጅ እርቀት ፍላጎትን አይገድብም

መሳይ ቀልቤሳ

አንዳንድ ቅን ኢትዮጵያውያን “የግንቦት 7 መሪዎች አውሮፓና አሜሪካ ተቀምጠው ወያኔን ለመጣል የሚያስችል ጠንካራ ትግል ለመምራት አይችሉም”ሲሉ እንሰማለን።አፈ ጮሌው ወያኔም ይህንን አስተያየት ቀልቦ በተለያዩ መድረኮች ላይ አቅርቦታል።ባገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ መሪዎች ሳይቀሩ ግንቦት 7ትን ለመተቸት የሚናገሩት ይህንን ነው።ቅን ኢትዮጵያውያን ጥያቄውን በተደጋጋሚ የሚያነሱት ለአገራቸው ካላቸው ፍቅር የተነሳና አሁን በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩ መሪዎች በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ለማምጣት ብቃቱ አላቸው ብለው ስለሚያምኑ ይመስለኛል ።የወያኔ መሪዎች አላማ ግን ግልጽ ነው፤የእንቅስቃሴው መሪዎች ወደ አገር ተመልሰው ያን የተለመደ የሰላማዊ ትግል መዝሙር እየዘመሩ እንዲኖሩ፤መዝሙሩን መዘመር እናቆማለን ካሉ ደግሞ በተለመደው መንገድ አደብ ገዝተው እንዲቀመጡ ለማድረግ ነው።ለማንኛውም ግን ጥያቄው ተገቢና ለውይይት የሚጋብዝ እንደሆነ ስለሚሰማኝ አንዳንድ አስተያቶችን ለመሰንዘር ደፍሬአለሁ።

አንድ ታጋይ ውጤታማ የሚሆነው የሚታገልበትን አላማ በጥራትና በብቃት ሲያውቅ፣ትግሉ የሚደረግበትን ጊዜና ቦታ መምረጥ ሲችልና የሁኔታዎችን መለዋወጥ እያየ ጥሩ አመራር ለመስጠት ዝግጁ ሲሆን ነው።የግንቦት ሰባት መሪዎችም አላማቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆናቸውን ከመርሀግብራቸውና ካለፈ ታሪካቸው መረዳት ይችላል።የትግሉን ጊዜና ቦታም በደንብ አስበውበት እንደመረጡ አምናለሁ።ወያኔን የመታገያው ጊዜ አሁን ካልሆነ መቼም ሊሆን አይችልም። የትግሉ ሜዳም የወያኔ ሰንሰለት ባለበት የምድር ዳርቻ ሁሉ ካልሆነ በየትም ቦታ ሊሆን አይችልም። የወያኔው መረብ በስፋት የተዘረጋው ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑም፣ዋናው የመታገያ ስፍራ የኢትዮጵያ ተራሮች፣ቋጥኞች፣ሜዳዎች፣ሸለቆዎች፣ወንዞች ወዘተ ናቸው። ግንቦት ሰባትም ተመሳሳይ እምነት እንደሚከተል አምናለሁ።

ዋናው የትግል ሜዳ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆን አለበት ሲባል መሪዎቹ የግድ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አለባቸው ማለት ግን አይደለም።መሪዎቹ ህይወታቸውን በሚያቆዩበትና ትግሉን ለረጅም ጊዜ ለመምራት በሚችሉበት ስፍራ ሊሆኑ ይችላሉ።ህይወታቸውን ለአደጋ በሚያጋልጥ ቦታ ሆነው ትግል እንምራ ቢሉ የራሳቸውንም የትግሉንም ህይወት በአጭር ይቀጫሉ።ይህንን ስል መሪዎቹ በህዝባቸው መሀል ሆነው መታገል የለባቸውም እያልኩ አይደለም።እንዲያውም በህዝብ መሀል ሆኖ መታገልን የመሰለ ጸጋ እንደሌለ አምናለሁ።ውዳሴውንም ትችቱንም እየሰሙ መታገል ፍሬውን ያማረ ያደርገዋልና።ዜኖፍ የተባለ ፈላስፋ አንድ መሪ በበጋው ጊዜ ጸሐዩን፣በክረምቱ ጊዜ ደግሞ ብርዱንና ዝናቡን የሚቋቋም፣የሚመራውን ህዝብ ደስታና ሀዘን ከመሀል ሆኖ የሚካፈል መሆን አለበት ይላል።

ከታሪክ እንዳነበብነውም በህዝባቸው መሀል ሆነው ትግሎችን የመሩ መሪዎች ለድል በቅተዋል።ታዋቂ የጦር መሪዎች የሚባሉት ታላቁ አሌክሳንደር፣አውግስቶስ ሴዛር፣ሳላ አዲን ፣ናፖሊዎን ቦና ፓርቲ፣ማኦ ሴ ቱንግ፣ሆቺሚኒ፣ቼ ጎቬራ፣ፊደል ካስትሮ፣ጀነራል ደጎል ወዘተ፣ባገራችን ደግሞ አጼ ካሌብ፣አጼ ዘረያቆብ፣አጼ ሱስንዮስ፣ አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ ፣አሉላ አባ ነጋ፣አጼ ሚኒልክ፣እቴጌ ጣሐይቱ፣ ጎበና ዳጩ፣ፊታውራሪ ሀብተጊዎርጊስ ዲነግዴ፣ በላይ ዘለቀ ወዘተ በተሰለፉበት ቦታ ሁሉ ድል ያደርጉ የነበረው በተዋጊዎቻቸው መሀል ሆነው ድንቅ አመራር በመስጠታቸው ነው።ይህን ስል አሁንም መሪዎቹ ለድል የበቁት የግድ በህዝባቸው መሀል ስለተገኙ ነው ማለቴ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ። ስታሊን፣ትሩማን ወይም ቸርችል የሁለተኛው የአለም ጦርነት ጀግኖች የተባሉት በእየአውደ ግንባሩ እየተገኙ ሰራዊታቸውን በመምራታቸው አልነበረም፤ተዋጊዎቻቸው የጠራ አላማ ስለነበራቸው የጠራ አላማ ካልነበራቸው ናዚስቶችን ተሸለው ስለተገኙ እንጅ።

የግንቦት ሰባት መሪዎቹ የግድ ወደ ኢትዮጵያ ካልሄዱ ድጋፌን አልሰጥም ብሎ የሚከራከር ፤ዶ/ር ብርሀኑ ወይም አቶ አንዳርጋቸው ክላሽንኮቭ ይዘው ሲዋጉ ካላየሁ እንደታጋይ አልቆጥራቸውም ብሎ የሚያምን ካለ ያ ሰው ክርክሩንና እምነቱን መፈተሽ ያለበት ይመስለኛል።

በመጀመሪያ ሰዎቹ የፖለቲካ መሪዎች እንጅ የጦር መሪዎች አይደሉም።የፖለቲካ ስራው መቆም ስለሌበትም የትም ሆነው መስራት ይችላሉ። አፍሪካን ነጻ ያወጡ መሪዎች ነጻ መሬት ከማግኘታቸው በፊት ይኖሩ የነበሩት በስደት ነው።ኬንያታ፣ንኩሩማ ና ሌሎችም መሪዎች ትግላቸውን የጀመሩት በእንግሊዝና አሜሪካ በስደት ላይ ሆነው ነበር።የደቡብ አፍሪካው ምቤኪና የኬንያው ራይላ ኦዲንጋ ስደት ላይ የነበሩና አሁን በስልጣን ላይ ያሉ መሪዎች ናቸው።የቲቤቱ ዳይለላማ አሁንም ስደት ላይ ሆነው ነው ቻይናን የሚያንቀጠቅጧት። ባጭሩ ሰዎችን መመዘን ያለብን ከያዙት አላማና ከሚሰጡት አመራር አንጻር እንጅ ከተቀመጡበት ቦታ ተነስተን መሆን የለበትም ።ስለዚህ በአሁኑ ሰአት መሪዎቹን ወደ አገራችሁ ካልገባችሁ ብሎ የሚተች ሰው፣አንድም የመሪዎች ህይወት እንዲቀጭ የሚመኝ ሰው ነው አልያም ወፍ ዘራሽ ፖለቲከኛ ነው ማለት ነው።

## መለስ፤ የፖሊሲያቸውን ውድቀት

፣ከገጽ 1 የዞረ

በዚሁ ጉባዔ ላይ መለስ” በኢትዮጵያ እየታየ ካለው የኢኮኖሚ እድገት ይልቅ፤የኤክስቴንሽን ሠራተኞች የዲፕሎማ ፍላጎት ይበልጣል” በማለት ይህን እንደ ስህተት መናገራቸው፤ ባንድ በኩል የኢኮኖሚ ዕድገት የሚባለው ነገር ከዲስኩር ያለፈ እንዳልሆነ ሲያመለክት፤ በሌላ በኩል ሚሊዮን ረሀብተኞችን በማፍራት ተወዳዳሪ ያልተገኘነት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ፤ምን ያህል ግለሰቦች በነፃነት ራሳቸውን ለመለወጥ እና ለማሻሻል ያላቸውን ፍላጎት እንደሚጨፈልቅ የሚያሳይ እንደሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ያስረዳሉ። መለስ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጡትን አስተያየት ሲያጠቃልሉም” ባለሙያዎቹ ለአርሶ አደሩ ፍቅር ከሌላቸው የተፈለገው ግብ አይመጣም” የሚል ድፍን ያለ ሎጅክ በማስቀመጥ ነው” ያሉት ታዛቢዎቹ፤”አላወቁትም እንጅ የግብርና ባለሙያዎቹም ራሳቸው እንኩዋን ሊወቀሱ ፖሊሲው ለረሀብና ለችግር የዳረጋቸው ናቸው ብለዋል። በሌላ በኩል ይህ ጉባዔ ከመካሄዱ በፊት በእያንዳንዱ

ድርጅት የተናጠል በተካሄደ ጉባዔ ብአዴን ተፈራ ዋልዋን ከምክትል ሊቀመንበር በማንሳት ደመቀ መኮነንን ሲተካ፤ ህወሀትም ነፃነት አስፋውን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት አስወግዷል።ተፈራ የተነሱበት ምክንያት ለጊዜው ያልታወቀ ሲሆን፤ ነፃነት የተነሱት የሚሊኒየሙ አስተባባሪ እንደመሆናቸው መጠን፤በሚሊኒየሙ የተጠበቀውን ምስል በአገሪቱ ሊፈጥሩ አልቻሉም ተብለው ነው።ወገን በአደባባይ በጥይት እየጨፈጨፉና እያስጨፈጨፉ ራሳቸው ያጠፉትን የ አገሪቱን ምስል ፤ነፃነት አስፋው ከየት እንደሚያመጡት እንቆቅልሽ ቢሆንም፤ ኢህአዴግ የራሱን ድርጅታዊ የበደል መስቀል፤ ተራ አባላቱን ማሸከም የለመደ ጨካኝ ፓርቲ በመሆኑ፤ እንደነ አሊ አብዶን ነፃነትንም መስቀል አሸክሞ አሰናብቷቸዋል።